# የአስመራው ቡድን ዛሬም "በአዞ እንባ" ስልት?

**ዘአማን በላይ** bzaman@yahoo.com

> *" አጣሪ ቡድኑ በሥራ ዘመኑ፣ የኤርትራ መንግስት በኢትዮጵያ፣ በጅቡቲ፣ በሶማሊያና በሱዳን የሚንቀሳቀሱትን ጨምሮ በቀጣናው የሚገኙ ታጣቂ ኃይሎችን እንደሚደግፍ አሳማኝ መረጃ ሰብስቧል፡፡ በኬንያ፣ በኡጋንዳ፣ በዩናትድ አረብ ኢምሬትስና በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ የኤርትራ የዲፕሎማሲ፣ የደህንነትና የህዝባዊ ግንባር ለፍትህና ለዴሞክራሲ (ህግደፍ) ደጋፊዎች ለተጠቀሱት ሀገሮች ታጣቂዎች ቀጥተኛ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡"*

ይህ አባባል የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ አይደለም – በመንግስታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥሮች 751 (1992) እና 407 (2009) መሠረት የኤርትራንና የኢትዮጵያን ሁኔታ ለማጣራት የተቋቋመው ቡድን በቅርቡ ያወጣው ሪፖርት እንጂ፡፡ መቼም ውድ አንባቢዎቼ ይህን አባባል በመግቢያነት የጠቀስኩት ያለ ምክንያት አለመሆኑን መገንዘባችሁ የሚቀር አይመስለኝም፡፡ አዎ! የሪፖርቱን ድምዳሜ በለሆሳስ ያነሳሁት፣ ከመሰንበቻው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሠራዊት ከኢትዮጵያ ድንበር ከ15 እስከ 18 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኙ ሦስት የኤርትራ የሽብርተኞች ማሠልጠኛ ማዕከላት ላይ የወሰደው ተመጣጣኝ የጥቃት ርምጃን ተከትሎ፣ የአስመራው ቡድን የበግ ለምድ ለብሶ በተኩላነት የሚያካሂደውን ማላዘን ግራሞትን አጭሮብኝ ነው፡፡

የአስመራው ቡድን ምስራቅ አፍሪካን የሁከትና የብጥብጥ አውድማ ለማድረግ የማተራመስ ስትራቴጂን ቀይሶ ለተግባራዊነቱ "ሌቱም አይነጋልኝ" ብሎ በመናወዝ የጥፋት እጆቹን መዘርጋቱን በዚህ ጽሑፍ አንባቢ ማውሳት "ለቀባሪው የማርዳት" ያህል ይሆንብኛል፡፡ ግና ለትውስታ ያህል ጥቂቶቹን የሽብር አውዶቹን ልጠቃቅምና ወደ ተነሳሁበት የመከላከያ ሠራዊታችን ስለ ወሰደው የጥቃት ርምጃ አጠቃላይ አንድምታን እንዲሁም የሻዕቢያውን ቡድን "የአዞ እንባ"ን ወደ መመልከቱ ላቅና፡፡

## አውደ-ሽብር

እንደሚታወቀው በአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ የሚመራው የኤርትራ መንግስት ሀገራችን ላይ በሽብር ሴራ የተተበተቡ የጥፋት እጆቹን መሰንዘር ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በተለይም "ሠላምና መረጋጋት ኢትዮጵያ ውስጥ የለም" የሚል አንድምታን ለመፍጠር በየማሰልጠኛዎቹ በአምሳያው ጠፍጥፎ የሚሰራቸው እንደ ኦነግ፣ ኦብነግ፣ ግንቦት 7 ወዘተ. የመሳሰሉ ተላላኪዎቹን እያስታጠቀ ወደ ሀገራችን አሰርጎ

በማስገባት ከልማት ጉዟችን ሊያሰደናቅፈን መጣሩ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡ ይሁንና ይህ ከንቱ ህልሙ በተለያዩ ጊዜያት በሠላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብና በጸጥታ ኃይሎች የተቀናጀ ጥረት ተላላኪዎቹ የተላኩትን የጥፋት መልዕክት ሳያደርሱ መንገድ ላይ እንዲቀሩ በመደረጋቸው ከስሟል፡፡ በዚህም ሳቢያ ሻዕቢያ ከአስመራ እስከ ሞቃዲሾ የዘረጋው የጥፋት መረብ መሃል ላይ እንዲበጣጠስ ተደርጓል፡፡

ታዲያ ይህ የአስመራው ቡድን "የጥፋት መለከት"ን ያዘለ ተግባር በተለያዩ ጊዜያት በሀገራችን ላይ ገቢራዊ እንዲሆን ሻዕቢያ ጀሌዎቹን አሰማርቶ ፍላጎቱ ስለመከነበት እጁን አጣጥፎ ተቀምጧል ማለት አይደለም፡፡ መቼም የአቶ ኢሳያስ ባለሚሎች ምልከታቸው ሁሉ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" የሚል በመሆኑ፣ ኢትዮጵያዊያንን ለማጥቃት ካላቸው ፍላጎት በመነሳት ባህር ተሻግረው ኡጋንዳ ውስጥ በአል- ሸባብ አማካኝነት "ኦፕሬሽን አስመራ" በሚል ስያሜ የኢትዮጵያዊቷን ማሜ መንገሻን ሆቴል በሲ- 4 ልቁጥ ፈንጂ እንዳልነበረ ማድረጋቸው ገፋ ቢል አንድ ዓመትን ብቻ የዘለለ ትውስታችን በመሆኑ የምንዘነጋው አይደለም፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ባለፈው ዓመት አጋማሽ ላይ 16ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ልዩ ጉባዔ ከመካሄዱ ቀደም ባሉት ቀናት "አዲስ አበባን እንደ ባግዳድ" ለማድረግ የኦነግ ጀሌዎችን አሰማርቶ፣ ሃሳቡ "የቀን ቅዠት" ሆኖ መቅረቱን ቀደም ሲል የጠቀስኩት የመንግስታቱ ድርጅት አጣሪ ቡድን አረጋግጧል፡፡ ቡድኑ በሪፖርቱ እንዳረጋገጠው፣ በወቅቱ በአስመራው መንግስት ላኪነት በመዲናችን ሊካሄድ የነበረው የሽብር ተግባር "በታክቲክ" ደረጃ ለየት ያለ ነበር፡፡ ይኸውም ድርጊቱ ንጹሐን ዜጎችን ሆን ብሎ ለማጥቃት ያለመና በሀገራችን ውስጥ ስጋት እንዲነግስ ለማድረግ የተጠነሰሰ መሆኑ ነው፡፡ ታዲያ ይህ እውነታ የአስመራው መንግስት "ለዳግማዊ ማዕቀብ" የዳረገው እንደነበር ዛሬ ላይ ሆኖ የሚዘነጋው አይመስለኝም፡፡

ሆኖም የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር በዓለም አቀፉ ህግ የሚሳለቅ በመሆኑ፣ ከለመደው የግብረ - ሽበራ ተግባር ምንም ዓይነት ማዕቀብም ሆነ ማስጠንቀቂያ ሊያግደው አልቻለም፡፡ በመሆኑም በያዝነው ዓመት "ኢትዮጵያ ውስጥ ሠላምና መረጋጋት የለም" ለማስባል የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ከመካሄዱ ቀደም ብሎ በአፋር ክልል አርታሌ አካባቢ በተላላኪ አሸባሪዎቹ አማካኝነት የሀገራችንን ሉዓላዊ ግዛት በመጣስ በሰላማዊ ቱሪስቶች ላይ ጥቃት ፈጽሟል፡፡ በዚህ እጅግ አረመኔያዊ ተግባሩም የአምስት ቱሪስቶችን ህይወት ቀጥፏል፣ ሌሎችም ታፍነው እንዲወሰዱ አድርጓል፡፡

እነዚህና ሌሎች ያልጠቀስኳቸውን በሻዕቢያ የሚቀነባበሩ "የሽብር አውዶችን" ለሰላም ካለው ቀናዒነት በመነጨ ከሚፈለገው በላይ ሲታገስ የነበረው የኢትዮጵያ መንግስት፣ ከአርታሌው ግብረ - ሽበራ ተግባር በኋላ ትዕግስቱ ሊሟጠጥ ችሏል፡፡ እናም የቱሪስቶቹን ህልፈተ - ህይወትና ጠለፋን ተከትሎ የአስመራው ቡድንና የግብረ -አበሮቹ ለፈጸሙት ተግባር ተመጣጣኝ የጥቃት ርምጃ እንደሚወስድ በይፋ ገልጿል፡፡

ታዲያ በወቅቱ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር "የዕቃ ዕቃ" ጨዋታ ዓይነት በቱሪስቶቹ ላይ ጥቃት የፈጸመው "አርዱፍ የተሰኘው ድርጅት ነው" የሚል መግለጫን በስላቅ መልክ ቢያወጣም ፣ በስም የተጠቀሰው ድርጅት "እኛ ኢትዮጵያ ውስጥ የምንፈልገው ዴሞክራሲታዊና ሰብኛዊ መብት የተከበረልን

በመሆኑ፣ በእንዲህ ዓይነት አሳፋሪ ተግባር ውስጥ ልንሳተፍ አንችልም“ የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡ የአቶ ኢሳያስ መንግስት ነገር “ዶሮን ሲያታልሏት” እንዲሉት ዓይነት መሆኑን በሚገልጽ ሁኔታ፡፡

## የተመጣጣኝ ጥቃቱ አንድምታ

ወታደራዊ ጠበብቶች እንደሚስማሙበት፤ “ተመጣጣኝ ጥቃት” ማለት ቀደም ሲል በጠላት ጦር የተሰነዘረን ጥቃት ድርጊቱን ብቻ ለይቶ ከጥቃቱ ጋር እኩል በሆነ ሁኔታ የሚሰጥ የአጸፋ ምላሽ ነው፡፡ ታዲያ ከዚህ አኳያ ሻዕቢያና ተላላኪዎቹ የፈጸሙትን የግብረ - ሽበራ ተግባር ለይቶ መመልከት ይቻላል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የሽብር አጋፋሪውም ሆኑ ጀሌዎቹ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ግዛት በተደጋጋሚ በመጣስ የአሸባሪነት ተግባራትን ፈጽመዋል – በተለይም በአፋር ክልል። ከዚህ በተጨማሪም በዚሁ ክልል የሀገራችንን ዜጎች አፍኖ በመውሰድ የእገታ ድርጊቶችን ማከናወናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ እነዚህ ተግባራትም በማናቸውም ዓለም አቀፍ የህግ ማዕቀፎች ተቀባይነት የሌላቸው ተራ ውንብድናዎች ናቸው፡፡

በዓለም አቀፉ ህግ መሰረት አንድ ሀገር ሉዓላዊነቷ ሲደፈር፤ ተመጣጣኝ የአጸፋ እርምጃ ልትውስድ ትችላለች፡፡ ለዚህም ነው የኢትዮጵያ መንግስት ተመጣጣኝ ጥቃት እንደሚወስድ ቀደም ሲል ያስታወቀው ፡፡ የሻዕቢያ ተላላኪዎች ከአፋር ክልል አቅራቢያ ከሚገኙት ማሰልጠኛ ማዕከሎታቸው እየተንደረደሩ ጥቃት በመሰንዘራቸው በምላሹ በአካባቢው በሚገኑ ማሠልጠኛዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ መውስድ የግድ ይላል፡፡

በዚህ መሰረትም ስመ - ጥሩና በሥነ - ምግባሩ የተመሰገነው ጀግናው የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት በአፋር ክልል አቅራቢያ በሚገኙትና ልዩ ስማቸው ራሚድ፣ ገላህቤን እና ጊምቢ በተሰኙ የሻዕቢያ የሽብርተኛ መፈልፈያ ጣቢያዎች ላይ እርምጃ ወስዷል፡፡ ይህ የመከላከያ ሠራዊታችን ፈጣንና ቅጽበታዊ ጥቃት የተካሄደው ከአፋር ክልል 15፣ 17 እና 18 ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ በሚገኙ ማሰልጠኛ ካምፖች ላይ በመሆኑ የእርምጃውን ተመጣጣኝነት የሚያመላክትና ተቀባይነት ያለው ራስን የመከላከል ተግባር ነው፡፡ ለምን ቢባል፤ እነርሱም ድንበር ጥሰው ጥቃት ያደርሱ ስለነበር ነው፡፡

የአንድ ሀገር መንግስት ዜጎቹን አፍነው የሚወስዱ ማናቸውንም ኃይሎች አደብ በማስገዛት የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አኳያ መከላከያ ሠራዊታችን የሀገሪቱን ዜጎች በኃይል አፍነው በወሰዱትና አቶ ኢሳያስ እንደ እንቁላል በሚፈልፍሏቸው ተላላኪዎች ካምፖች ላይ የወሰደው ርምጃ ተመጣጣኝ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ምክንያቱም ሽብርተኞቹ የሚገኙት ኢትዮጵያን እንደ ጠላት በሚመለከታት መንግስት ምድር ላይ ስለሆነ፤ እነርሱን በቀጥታ ይዞ ለፍርድ ማቅረብ ስለማይቻል ነው፡፡ በመሆኑም የሚገኙበት አካባቢ ሄዶ ቀጥተኛ ጥቃት መሰንዘር ብቸኛው አማራጭ ይሆናል ማለት ነው፡፡ እናም የመከላከያ ሠራዊታችን ጥቃት ሚዛናዊ፣ እንደ አሸባሪዎቹ ንጹሃን ዜጎች ላይ ያላተኮረ እና የሻዕቢያን “የሽብር ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችን” ብሎም አሸባሪዎቹን ብቻ ነጥሎ የመታ ተመጣጠኝና ተገቢ እርምጃ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

# ዛሬም "በአዞ እንባ " ስልት?

አስመራም ይሁን ምጽዋ የሚገኙት የአቶ ኢሳያስ ቤተ - መንግስቶች ውስጥ የሚገኘው መዝገበ-ቃላት የተሞላው በማደናገሪያ ስልት ነው፡፡ የኤርትራ ገዥዎች እውነትን ከተናገሩ በስርቅታ የሚሞቱ ይመስል፤ የውሸት ድርሳን መከሸንን እንደ ዕለት እንጀራቸው የሚቆጥሩት ተግባር ነው፡፡ ታዲያ በአቶ ኢሳያስ የሚመራው የአስመራው ቡድን እውነትን አምርሮ የሚጠላ ለመሆኑ በርካታ አስረጂዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ግና ከተነሳሁበት ነጥብ አኳያ ቡድኑን እንደ ዥዋዠዌ የሚዋዥቀው አቋሞች መካከል ሁለት ሰበዞችን ብቻ በመንቀስ መመልከቱ፤ የሻዕቢያን የ"አዞ እንባ" ስልት በግልጽ ለመረዳት ይጠቅማል፡፡

በኤርትራ መንግስት እምብዛም በማይታመኑት በአቶ ኡስማን ሳላህ የሚመራው የዚያች ሀገር የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት፣ ሰሞኑን መከላከያ ሠራዊታችን የወሰደውን ጥቃት አስመልክቶ ትናንትን የረሳ እጅግ አስገራሚ መግለጫ አውጥቷል፡፡ መግለጫውም "...በኢትዮጵያ መንግስት የተፈጸመው ጥቃት የኤርትራን ሉዓላዊ ግዛት በመድፈር የተፈጸመ በመሆኑ በመንግስታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት በኢትዮጵያ ላይ እርምጃ እንዲወስድልን እጠይቃለን ..." የሚል ነው፡፡

እርግጥ ማንም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ፤ ይህ የቃላት ትወና ትናንት የመንግስታቱን ድርጅት "አሰራሩን መቀየር አለበት፣ በጥቂት ኃይሎች የሚዘወር ነው... ወዘተ" በማለት ሲያጣጥሉትና ሲያወግዙት ከነበሩት የኤርትራው "የነውጥ አጋፋሪዎች" የተሰነዘረ መሆኑን ሊጠራጠር ይችላል፡፡ ግና እወነቱ ይኸው ነው – የመግለጫው ባለቤት ትናንት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት "አተረማመሰው፣ ከባቢያችንን አመሰው" በማለት ከሰዋቸው፣ "የአሜሪካ ኤምባሲ ቪዛ ከለከለኝ" በሚል የተለመደ ማደናገሪያ ፀጥታው ምክር ቤት ተገኝተው ምላሽ ለመስጠት ያልፈለጉት አቶ ኢሳያስ ናቸው፡፡ ታዲያ ዛሬ ምን ታይቷቸው ይሆን፣ የመንግስታቱን ድርጅት መማጸናቸው?...እናንተዬ ማን ነበር የማያውቁት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ያለው እንስሳ?...

ያም ሆነ ይህ ግን፤ እርሳቸውም ተማጸኑ፣ አልተማጸኑ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እውነታውን በሚገባ ያውቀዋል፡፡ ትናንት የኢትዮጵያን አሸባሪዎች እንደ አሮጌ ዕቃ ከወዳደቁበት ለቃቅመው እየመለመሉ በመላክ ሉዓላዊነታችንን እንዳልተዳፈሩ ሁሉ፤ ዛሬ በተመጣጣኝ እርምጃ የአሸባሪዎቹ መፈልፈያ ኩሬ ሲመታ መጮህ ትርጉም አልባ መሆኑን የትኛውም ወገን የሚረዳው ሃቅ ነው፡፡ ይሁንና የሻዕቢያው ቁንጮ ለቅጽበት ሰከንዶች ተራ ፕሮፖጋንዳ የሚጠቅማቸው እስከሆነ ድረስ "የአዞ እንባ" ማንባት ልማዳቸው ስለሆነ የሚደንቀን አይሆንም፡፡

ትናንት ሁለተኛ ማዕቀብ ሲጣልባቸው ስድስቱ የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት (ኢጋድ) ሀገሮች "እያወኩን ነው" ሲሏቸው "የዓይኔን ግንባር ያድርገው" ድርቅናቸው እንዳልሰራ ሁሉ ፤ ዛሬም የእጃቸውን ሲያገኙ በሰበብ አስባቡ ማላዘን የማያወጣ መሆኑን ዋናው ሰውዬም ሆኑ በዙሪያቸው የሚያጫፍሩት ባለስልጣናት መገንዘብ ያለባቸው ይመስለኛል፡፡

በአቶ ኢሳያስ መንግስት ለመገናኛ ብዙሃን የተሰጠው ሌላው አስቂኝ አባባል ዕውነታውን የሚያውቁ ሰዎችን ያስደመመ ነው፡፡ የማስታወቂያ ሚኒስትሩ አቶ አሊ አብዱ ከመሰንበቻው ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ "...ኤርትራ በጎረቤት ኢትዮጵያ ላይ የአጸፋ ምላሽ አትወስድም" ሲሉ መናገራቸው፤ እርግጥም ሃቁን የሚያውቁ በርካታ ወገኖችን ፈገግ ማሰኘቱ አልቀረም ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የአቶ አሊ "ኮሚክ" ዲስኩር የአስመራውን ቡድን ለሠላም የተጋ አስመስሎ የማቅረብ ተራ ፕሮፓጋንዳ መሆኑን ራሳቸውንም ቢሆኑ እንደለመዱት ከተናገሩ በኋላ ትዝ ሊላቸው ይችል ይሆናል፡፡ ግና እውነታው "የሚሉሽን በሰማሽ፣ ገበያ ባልወጣሽ" እንዲሉት ዓይነት በመሆኑ፤ መቼም ቢሆን የአስመራው ቡድን ለሠላም ተግቶ እንደማያውቅ የመንግስታቱ ድርጅት አጣሪ ቡድን በሚገባ ያውቀዋል፡፡

እናም የዕውነታው ጓዳ ሲገለጥ ነገሩ ለእነ አቶ አሊ "ጽድቁ ቀርቶ፣ በወጉ በኮነነኝ" እንዲሉት ሳይሆን የሚቀርባቸው አይመስለኝም፡፡ ለምን ቢባል፤ የሻዕቢያው ቡድን እንኳንስ ስለ ሠላም ሊያስብ ቀርቶ፣ "የሠላም" የሚለውን ቃል ሲሰማ የሚበረግግ መሆኑ ስለሚታወቅ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ተጨባጩ ምክንያት፤ ስለ ሠላም የሚያስብ ማንኛውም ኃይል የቀጣናውን አሸባሪዎችና ጸረ - ሠላም ኃይሎች በጉያው ውስጥ ወሽቆ በንፁሃን ደም "እልል በቅምጤ " እያለ በመጨፈር የሀገራቱን ሠላም ሰለማያውክ ነው፡፡ ታዲያ ዓለም የሚያውቀው ሃቅ ይህ ሆኖ ሳለ፤ የሻዕቢያዊያን ለሰላም አሳቢ የመሆን "የቀበሮ ባህታዊነት" ከቶ ከየት የመጣ ይሆን?– እንደተመደው ዛሬም ያለ ምንም ስትራቴጂ ለውጥ ባረጀ ባፈጀ ተራ የመንደር ዱርዬ ተግባር ለመከወን ካልፈለገ በስተቀር፡፡

የአቶ አሊ "ኤርትራ በኢትዮጵያ ላየ የአጸፋ ምላሽ አትወስድም "አባባል፤ በእርሳቸው ያልበሰለ ፕሮፓጋንዳ ለመግለጽ እንደተሞከረው ኢትዮጵያ የኤርትራ ጎረቤት ስለሆነች አይደለም፡፡ እርግጥ የማስታወቂያ ሚኒስትሩ ያልካዱት ነገር ሀገራችን የኤርትራ ጎረቤት መሆኗን ብቻ ነው (በተጣባቸው የውሸት ፖለቲካ ይህንንም መካድ ቢችሉ ደስተኛ እንደሚሆኑ ልብ ይሏል!) ግና ምን ያደርጋል?-የአፍሪካን ካርታ ቀደው አይጥሉት ነገር።

ያም ሆነ ይህ ግን፤ የኤርትራ አጸፋ ምላሽ ያለመስጠት ምክንያት ይህ አይደለም፡፡ ማንኛውም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው ላለፉት 20 ዓመታት እንደ ካሮት ቁልቁል ሲያድግ የነበረው የኤርትራ ኢኮኖሚ ላሽቋል፣ የሀገሪቱ ሠራዊት በየጊዜው ሥርዓቱን እየከዳ ወደ ጎረቤት ሀገሮች ከመሸሹም በላይ፣ የመዋጋት ሞራሉ ወድቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኤርትራ ህዝብና ከ20 የማይበልጡ የሻዕቢያ ሹማምንቶች "ሆድና ጀርባ" ናቸው፡፡

ታዲያ በእነዚህ ሁኔታዎች አጣብቂኝ ውስጥ የሚገኘው የኤርትራ መንግስት ምናልባት 'የአጸፋ ምላሽ እሰጣለሁ' አሊያም 'ወደ ሙሉ ጦርነት እገባለሁ' ብሎ ቢሞክር ምን ሊከተለው እንደሚችል ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ይኸውም ያለው ኢኮኖሚ የሚያስበውን የጠብ ጫሪ ጦርነትን ሊሸከመው የማይችል፣ ሠራዊቱ የሀገሪቱ ጄኔራሎች እርሻ "የቀን ሰራተኛ" በመሆኑ በማንኛውም ወቅት ሸርተት ሊል የሚችል እንዲሁም ለአንድ የጦርነት ድርጊት ወሳኝ የሆነው የህዝብ ድጋፍ ኤርትራ ውስጥ የነጠፈ በመሆኑ ትርፉ ራስን በራስ የማጥፋት ያህል ነው፡፡ በመሆኑም አቶ ኢሳያስ የአጸፋ ምላሽ ቢሰጡ፤ በምላሹ የኢትዮጵያ መንግስት

ለእያንዳንዱ የሻዕቢያ ትንኮሳ ተመጣጣኝ እርምጃ ስለሚወሰድ በአንገታቸው ላይ ሽምቀቆ ማስገባት ስለሚሆን ፤ይህን ተግባር ይፈጽሙታል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ይህ ማለት ግን የአስመራው ቡድን እንደ ሱስ ከተጠናወተው የሽብር ተግባር ተቆጥቦ እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል እያልኩ አለመሆኑን ወድ አንባቢዎቼ እንደምትገነዘቡልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ አዎ! የኤርትራ መንግስት በጀብደኝነት ስሌት የሚንቀሳቀስ በመሆኑ፤ ምናልባትም "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" በሚል የሞኝ ብሂል ሊውተረተር ይችላል፡፡ ይሁንና ያኔ በራሱ ላይ እባብ በመጠምጠም ወደ ግብዓተ - መሬቱ የሚሄድበትን ጊዜ እያፋጠነ ለመሆኑ መጠራጠር ያለበት አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ከኢትዮጵያ መንግስት አቋም አንጻር፤ የአስመራው ቡድን ወደ ሙሉ ጦርነት እገባለሁ ብሎ ካሰበ ለሦስተኛ ጊዜ ጦርነት እንዳይከፍት ተደርጎ ሊመታ ስለሚችል ነው፡፡ ታዲያ ያኔ የኤርትራ መንግስት ጉዳይ "የውሾን ነገር ያነሳ ውሾ" እንዲሉት ዓይነት ዳግም ላይመለስ ተረስቶ የመቅረት ዕጣ ፈንታ ፅዋውን ማንሳቱ አይቀሬ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

## ነገስ ምን ይሆናል?

የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር የዛሬን የሽብር ወላፈን በመሞቅ የሚኖር የግብዞች ስብስብ ነው፡፡ 'ነገ ምን ይከተለኛል' የሚል መንግስታዊ ቀመር እንኳን መስራት የሚችል አይደለም፡፡ ሁሌም በሳህል ተራራ የጫካ ህግ ጀብደኝነት የሚመራ ስለሆነ፤ ትናንትን እንጂ፤ ነገን አያስብም፡፡ በሌላ ማንነቱም እየተንጠራራ፤ እርሱ በዔሊነት እየተንፏቀቀ በዲፕሎማሲ፣ በፖለቲካ፣ በወታደራዊነ በኢኮኖሚ መስሶች እንደ ጥንቸል የሚቀድሙትን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራትን ለማሸበር መጣሩን እንደ "አልፋና ኦሜጋ" መርህ መከተሉ ትናንት የነበረ፣ ዛሬም ያለና ነገርም የሚኖር እውነት ነው፡፡

ታዲያ ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ለእነዚህ የሽብር ተግባራቱ ሁነኛ መፍትሄ በሀገራችን መንግስት በኩል ተቀምጧል፡፡ አዎ! በአፋር ክልል ለፈጸመው የግብረ - ሽበራ ድርጊት፤ በዚያው አካባቢ በሚገኙ አሸባሪዎችና ካምፖቻቸው ላይ በሦስት ቦታዎች መከላከያ ሠራዊታችን አጸፋዊ እርምጃ ወስዶ በሠላም ወደ መደበኛ ቦታው እንደተመለሰው ሁሉ፤ይህን መሰሉ ተገቢና ተመጣጣኝ ቅጣት ይቀጥላል፡፡

እንደሚታወቀው ሠላም ወዳዱ የኢትዮጵያ መንግስት የአስመራው ቡድን ለይስሙላ ለሚያነሳው የድንበር ውዝግብ በሠላምና በድርድር መፈታት እንዳለበት ባለ አምስት ነጥብ የሠላም ሃሳብን ያለመታከት በተደጋጋሚ አቅርቧል፡፡ እንዲያውም ከግማሽ መንገድ በላይ በመሄድ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ከአስመራው ቡድን ጋር ተወያይቶ አለመግባባቱን ለመፍታት ዝግጁ መሆኑን አሳውቋል–እስካሁን ድረስ የሚሰማው ባያገኝም።

ዳሩ ግን ሻዕቢያ ነገም በጀብደኝነት እሳቤ እንደ ትናንቱ ሠላምና መረጋጋታችንን ለማደፍረስ ከተንቀሳቀሰ፣ እያንዳንዱ የሠላም ቀን ለእኛ ዋጋ ያላት በመሆኗ መንግስታችን እግር በእግር እየተከታተለ ተገቢውን ተመጣጣኝ እርምጃ መውሰዱ አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ አቶ ኢሳያስም ሆኑ አጋፋሪዎቻቸው በተለያዩ የፊት ለፊት አውደ ውጊያዎችም ይሁን በወታደራዊ ዲፕሎማሲ የተሰጠውን ተልዕኮ የመፈፀም

አቅሙን ጠንቅቀው የሚያውቁት መከላከያ ሠራዊታችን ሁሌም ዝግጁ ሆኖ እያንዳንዷን ኮሽታ እየተጠባበቀ ነው፡፡

እናም የኤርትራ መንግስት አጠቃላይ ሁኔታ ከዚህና ቀደም ሲል ከጠቀስኳቸው ውድቀቶቹ አኳያ ሲታይ “ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥ” እንዲሉት ዓይነት መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ ስለሆነም “የአዞ እንባ” ስልቱ ጊዜ ያለፈበት ተራ ወሬና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም “የተበላ ዕቁብ” የሚሉት ዓይነት መሆኑን ስለሆነ ማላዘኑ እንደማያዋጣው በማወቅ የሠላምን በር ቢያንኳኳ በጄ ነው፡፡ አሊያ ግን ኢትዮጵያዊያን ለሰላም ልዩ ክብር ሰጥተው “በጥባጭ እያለ ማን ጥሩ ይጠጣል” እያሉ በመከላከል ስትራቴጂ ብቻ ሻዕቢያን የሚያስታምሙበት ወቅት በመርፈዱ፣ የሠላም ሰንደቃቸውን በሻዕቢያዊያን ውድቀት ላይ ማንበልበላቸው የሚቀር አይመስለኝም፡፡